


# የልጆችን ደህንነት መጠበቅ።

ካቶሊክኬር የልጆች ደህንነት ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነው።

በካቶሊክኬር ሁሉም ልጆች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት ብለን እናስባለን። ልጆች ላይ የሚደርሰውን በደል ለመለየት፣ ለመከላከል እና ሪፖርት ለማድረግ በትጋት እንሰራለን። ልጆች ደህንነታቸው እየተጠበቀ እንዳልሆነ ስናውቅ ተገቢውን እርምጃ እንወስዳለን።

የሚከተሉትን በማድርግ የልጆችን ደህንነት እናጠናክራለን

- ልጆችን በማዳመጥ።
- ቡድናችን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለምሳሌ ያክል የሰራተኞችን፣ የተቋራጮችን፣ የበጎ ፈቃደኞችን እና የቦርድ አባላትን የኋላ ታሪክን መፈተሽ (ከልጆች ጋር መሥራት፣ የፖሊስ እና የማጣቀሻ ምስክሮች)።
- ሁሉንም ሰራተኞች፣ ተቋራጮች እና የበጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች በልጆች ደህንነት ዙሪያ ላይ በመስመር ላይ እንዲሁም በአካል የሚሰጠውን ቀጣይነት ያለውን ሥልጠና ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ።
- ከልጆች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞችን ባሕርይ እና የስራ አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ።
- ሕፃናትን የሚያካትቱ እና አደጋዎችን ሊያደርሱ የሚችሉ ሁሉንም ተግባራት መገምገም እና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ።
- ሰራተኞቻችን፣ የስራ ቦታዎቻችን እና ድረ ገጾች ለህፃናትን ደህንነት የማያሰጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- ለሁሉም የቡድናችን አባላት ተደራሽ የሆኑ ሪፖርት የማድረጊያ ሂደቶች እና መገልገያዎች እንዲኖሩ ማድረግ።
- የሕፃናትን ደህንነት፣ ብቃት እና ተሳትፎን ማሳደግ ዋና ተግባሩ የሆነ የሥራ ቡድን ማዋቀር።
- ሁሉንም በሕግ የተጣሉብንን ግዴታዎች ለማሟላት መሥራት።
- አሁን ያለንን የልጆችን ደህንነት የሚጠብቀውን ባህል ማዳበር እና አጠናክሮ መቀጠል።

አስተያየቶችን በደስታ እንቀበላለን እንዲሁም ስለ ማናቸውም የህፃናት ደህንነት ስጋት ካለዎት እንዲነግሩን እናበረታታዎታለን።

የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የገባነውን ቁርጠኝነት የሚያሳየውን መረጃ ቅጅ ለማግኘት የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎበኙ www.ccam.org.au/childsafe